# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 237927

ጥቅምት 2 ቀን 2016 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንደሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነጻነት ተገኝ

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ ምስራቅ ማሞ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች** ፡- 1ኛ. አቶ ሰለሞን ማሞ

2ኛ. ወ/ሮ ገነት ማሞ

3ኛ. አቶ ወንዳፕር ማሞ

4ኛ. ወ/ሮ ሂሩት ማሞ

(1ኛ–4ኛ) - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የውርስ ሀብት ክፍፍልን የተመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ በቤንች ሸካ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲጀምር የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ/ም ጽፈው ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ የውርስ ንብረት የሆኑት በአማን ክ/ከተማ ኮመታ ቀበሌ ሜዳ ሰፈር እና ቄራ ሰፈር የሚገኙ ቤቶች የውርስ ሀብት የሆኑና ቀደም ሲል በነበረ ክርክር ለሁለት ወራሾች ድርሻቸው ተሰጥቶ የተጠቀሱት ቤትና ይዞታ ሳይከፋፈል በተጠሪዎች ዕጅ ስለሚገኝ የድርሻየን እንዲያካፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ በክሱ የተጠቀሱት ቤቶች የውርስ ንብረት መሆናቸውን አንክድም፤ ከአመልካች ጋር ተገናኝተን የድርሻዋን ለመስጠት ብናስጠይቃትም እምቢተኛ የሆነችው ራሷ ናት፤ ድርሻዋን ለመስጠት ፈቃደኛ ነን፤ ንብረቱ በባለሙያ ተገምቶ ድርሻዋን በገንዘብ እንድንከፍል ይወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች የውርስ ንብረት የሆኑት ቤቶች በእጃቸው የሚገኙ መሆኑንና ለአመልካች ድርሻዋን ለመስጠት ፈቃደኛ ነን በማለት ክሱን ሙሉ በሙሉ አምነዋል፤ ቤትና ይዞታውን ቢቻል በአይነት እኩል እንዲካፈሉ ካልተቻለም ንብረቶቹ በባለሙያ ተገምተው የአመልካችን ድርሻ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ በማለት ሰኔ 15/ 2014 ዓ.ም በዋለ ችሎት ወስኗል፡፡

አመልካች ንብረቶቹ መካፈል ካልቻሉ በባለሙያ ተገምተው ድርሻዋን ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ተብሎ መወሰኑን በመቃወም ይግባኝ ለደቡብ ምዕ/ኢት/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም በአብላጫ ድምጽ ውሳኔው የፀና ሲሆን ለክልሉ ሰበር ችሎት ያቀረቡት አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ህዳር 27 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ የስር ፍ/ ቤት ንብረቱ በዓይነት ሊካፈል እንደሚችልና እንደማይችል ያደረገው ማጣራት የለም፤ ንብረቶቹ ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ በዓይነት ማካፈል አይቻልም፤ ስለሆነም በውሳኔው መሰረት የውርስ ሀብት ክፍፍል የሚደረገው በባለሞያ ተገምቶ ነው፤ ይህም የሚመለከተው የግንባታ ወጪ ዋጋን (book value) በመሆኑ ግምቱ ወቅታዊ የገበያ ዋጋን (markete value) መሰረት ያላደረ ስለሚሆን አመልካችን በእጅጉ ይጎዳል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1083 እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 8 በሰ/መ/ቁ 40510 በቅጽ 19 በሰ/መ/ቁ 103049 እና በቅጽ 18 በሰ/መ/ቁ 102932 የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ይታረምልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1086 እና 1087(1) መሰረት ክፍፍል የሚደረገው እያንዳንዱ ወራሽ ከውርስ ውስጥ ንብረት እየተሰጠ በዓይነት ስለመሆኑና በዓይነት የተመደቡት ድርሻዎች ትክክል ያልሆነ እንደሆነ ተጨማሪ ገንዘብ በመስጠት እደሚስተካከል፤ እንዲሁም የድርሻዎቹን አመዳደብ ስርዓትም በተቻለ መጠን ለእያንዳንዱ ወራሽ በሚሰጠው የጎላ ጠቀሜታ መሰረት ተደርጎ ሊከናወን እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በዓይነት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሚደረግ ክፍፍል ቀዳሚ የክፍፍል ስርዓት ስለመሆኑ ከእነዚህ የህግ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የውርስ ሀብት ክፍል በሀራጅ በመሸጥ ክፍፍል የሚደረገው በልዩ ሁኔታ በዓይነት ንብረቶችን ማካፈል ካልተቻለ ብቻ ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ክርክር የተነሳበት የውርስ ሀብት ክፍል በዓይነት ይካፈል በማለት የሰጠው ውሳኔ በህጉ አግባብ የተሰጠ ነው፡፡ በዓይነት ማካፈል ካልተቻለ የንብረቱ ግምት በወቅቱ የገበያ ዋጋ ቢገመት የአሁን ተጠሪዎች አንቃወምም፡፡ በመሆኑም በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ውሳኔው ሊፀና ይገባል ብለዋል፡፡

አመልካችም ክርክራቸውን አጠናክረው ንብረቱ በአይነት መካፈል ካልተቻለ በባለሙያ ተገምቶ ግምቱን ከፍለው ይውሰዱ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተሻሽሎ በአይነት መካፈል ካልተቻለ ህጉ ባስቀመጠው የውርስ ክፍያ ደንብ መሰረት እንዲፈፀም ይወሰንልኝ በማለት የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችን ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው ግራቀኙን እያከራከረ ጉዳዩ እስከዚህ ፍርድ ቤት የደረሰው የውርስ ሀብት የሆነውን ቤትና ይዞታ በአይነት መክፈል ካልተቻለ ንብረቶቹ በባለሙያ ተገምተው የአመልካችን ድርሻ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ በመባሉ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ የውሳኔ ክፍል የውርስ ንብረት ሊከፋፈል የሚገባበትን በህጉ የተዘረጋ የክፍፍል ስርዓት ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን ተመልክተናል፡፡

የውርስ ንብረት ክፍፍል አሰራር የሚከናወንበት መንገድ በፍትሐብሔር ሕጉ ተመልክቷል፡፡ የውርስ ንብረት ክፍፍል አሰራር በወራሾች መካከል በሚደረግ ስምምነት፤ ወራሾች ያልተስማሙ እንደሆነ ከእነርሱ መካከል አንዱ ተግቶ ያሰናዳው የክፍያ ሐሳብ እንዲፀድቅ ለዳኞች ቀርቦ በሚጸድቀው አግባብ ሊከናወን እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1079 ስር ተደንግጓል፡፡ የመከፋፈሉ አፈፃፀም ደንብም በቁጥር 1082 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት ክፍያው የሚፈፀመው ሟቹ በፃፈው የኑዛዜ ቃል እንደሆነ፤ ስለክፍያው አፈፃፀም የተፃፈ ኑዛዜ ቃል ከሌለ ደግሞ በሕጉ በተዘረጋ ስርዓት መሰረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ የክፍፍሉ ደንብ በሕጉ የሚከናወንበት አግባብም ከቁጥር 1083 ጀምሮ ተመልክቷል፡፡ እነዚህ ስለውርስ ንብረት ክፍፍል የሚደነግጉት ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት ሲታይ ክፍፍሉ በዓይነት እንዲሆን ማድረግ ቀዳሚ የክፍፍል ሥርዓት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ የውርስ ንብረት ወራሾች በአይነት እንዲከፋፈሉ ማድረግ ቅድሚያ የሚፈጸም የክፍፍል ስርዓት ቢሆንም ካልተቻለ ወይም ስለክፍፍሉ ስምምነት ከሌለ ቀጥሎ የሚሆነውን ስርአት መለየት ያስፈልጋል፡፡

በእርግጥ ከወራሾቹ አንዱ ወይም ሌላው ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ በመፈለጉ ብቻ ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ ሊደረግ እንደማይገባ ከህጉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሕጉ የውርስ ንብረት ክፍፍል በአይነት የመከፋፈል ስርዓት በቅድሚያ እንዲከናወን ፍላጎቱ ነው፡፡ ከዚህ አልፎ የውርስ ንብረት በሐራጅ የመሸጥ ስርዓት ተግባራዊ የሚሆንበት አግባብ በሕጉ አንቀጽ 1092 ስር የተመለከተ ሲሆን ይህም የሚሆነው የውርስ ሀብት ውስጥ ከፍ ያለ ጉዳት ሳይደርስባቸው ሊከፈሉ የማይችሉ ንብረቶች ያሉ እንደሆነና ከወራሾቹ መካከል ይህን የማይከፈል ሀብት ሊወስድ የሚገባው የትኛው እንደሆነ በስምምነት ለመወሰን ያልቻሉ ከሆነ ስለመሆኑ ድንጋጌው ያሳያል፡፡ በተከታዩ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ድንጋጌ አንቀጽ 1093 ስር እንደተመለከተውም ከወራሾቹ መካከል አንደኛው ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ ሽያጩ በወራሾች መካከል በሐራጅ ሊደረግ እንደሚገባ፤ በወራሾች መካከል ስምምነት ከታጣም በሐራጅ ጨረታ ውስጥ ባዕድ ሰዎች እንዲገቡ ሊደረግ እንደሚገባ በቅደም ተከተል አስቀምጧል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የበላይ ፍርድ ቤቶች የውርስ ሀብት የሆኑት ቤቶችና ይዞታ በአይነት መካፈል ካልተቻለ ንብረቶቹ በባለሙያ ተገምተው የአመልካችን ድርሻ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ በማለት የሰጡት ውሳኔ ከላይ የተመለከቱትን የውርስ ሕጉን ድንጋጌዎች ይዘት ሙሉ በሙሉ የተከተለ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የውርስ ንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ የሰጡት ውሳኔ ሊቃና ይገባል ብለናል፡፡

በአጠቃላይ የውርስ ንብረት የሆነው ቤትና ይዞታ ቢቻል በአይነት እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ቢሆንም በአይነት እኩል መካፈል ካልተቻለ ንብረቶቹ በባለሙያ ተገምተው የአመልካችን ድርሻ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በውርስ ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያልተከተለ እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 94322 እና በሌሎች ተመሳሳይ መዛግብት የሰጠውን ትርጉም ያልተከተለ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 222670 ሰኔ 15 ቀን 2014 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፤ የደቡብ ምዕ/ኢ/ህ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11778 ጥቅምት 10 ቀን 2015 ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 12140 ህዳር 15 ቀን 2015 ዓ/ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአማን ክ/ከተማ ኮመታ ቀበሌ ሜዳ ሰፈር እና ቁራ ሰፈር የሚገኙ የውርስ ቤቶች በግራቀኙ መካከል በአይነት እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ በአይነት መክፈል ካልተቻለ በግራቀኙ ስምምነት መሰረት፤ ስምምነት ከሌለም በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሰረት ተገምቶ እንዲቀርብ በማድረግ በዚህ ግምት መነሻነት በወራሾች መካከል ሀራጅ ተደርጎ ድርሻቸውን እንዲያገኙ፤ በወራሾች መካከል ሀራጅ ማድረግ ካልተቻለም የባዕዳን ሀራጅ ተደርጎ የሽያጩን ዋጋ እኩል ሊከፋፈሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡ በዚህ መሰረት ይፈፀም፡፡
3. ለሰበር ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፅ/ወ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !